BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## How much is this?
## ስንት ነው?

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያንን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል ሱቅ ገብተው ዕቃ በሚገዙበት ጊዜ ዋጋ እንዴት እንደሚጠይቁ ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች ሱቅ ውስጥ ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

***Fiona***
*Hi, how much is this jacket?*

***Shop assistant***
*That jacket's £59.99.*

***Fiona***
*Can I try it on?*

***Shop assistant***
*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። በመጀመሪያ ፊዮና ፊዮና 'ይህ ጃኬት ዋጋው ስንት ነው?' 'How much is this jacket?' ስትል ጠየቃለች። አንድን ነገር ብቻ በተመለከተ ስናወራ 'this' የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። ከአንድ በላይ ስለሆኑ ነገሮች ስናወራ ግን 'these' የተባለውን ቃል እንጠቀማለን። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*Hi, how much is this jacket?*

**ዘሩባቤል**
በመቀጠል የሱቁ ረዳት 'That jacket is…' ብሎ ዋጋውን በማስከተል መለሰ። ዋጋ የሚገለፀው ከነጥብ በፊት እና በኋላ ያሉትን አሃዞች አነጣጥሎ በመናገር ነው። ስለዚህም 59.99 'fifty-nine ninety-nine' ሃምሳ ዘጠኝ ከዘጠና ዘጠኝ ይሆናል። 20.50 'twenty fifty' ደግሞ ሃያ ከሃምሳ ይሆናልማለት ነው። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*That jacket's £59.99.*

**ዘሩባቤል**
በመቀጠል ፊዮና መሞከር እችላለሁ? 'Can I try it on?' ስትል ጠይቃለች። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Can I try it on?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
በመጨረሻም የሱቁ ረዳት 'በሚገባ፤ ትችያለሽ' 'Of course you can.' ብሎ መልሷል። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች ሱቅ ውስጥ ሲነጋገሩ በማዳመጥ ከእርሶ መልስ ጋር ያወዳድሩ።

*Hi, how much is this sweater?*

*That sweater's £24.99.*

*Can I try it on?*

*Of course you can.*

*Hi, how much is that coat?*

*This coat is £39.99.*

*Can I try it on?*

*Of course you can.*

*Hi, how much are these shorts?*

*Those shorts are £19.99.*

*Can I try them on?*

*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፥ ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። አሁን እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጣሉ።

*Hi, how much is this jacket?*
*Hi, how much is this jacket?*

*That jacket's £59.99.*
*That jacket's £59.99.*

*Can I try it on?*
*Can I try it on?*

*Of course you can.*
*Of course you can.*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታውሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*ጃኬቱ ስንት ነው?*
*Hi, how much is this jacket?*

*ጃኬቱ ሃምሳ ዘጠኝ ከዘጠና ዘጠኝ ነው።*
*That jacket's £59.99.*

*መሞከር እችላለሁ?*
*Can I try it on?*

*በሚገባ*
*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሱቅ ውስጥ የአንድ ዕቃ ዋጋ ስንት እንደሆነ መጠየቅ ይችላሉ። ከሱቁ ረዳት ጋር ያለውን ውይይት ይለማመዱ። የሸሚዙን ዋጋ እና መሞከር ይችሉ እንደሆነ ይጠይቁ።

*That shirt's £19.99.*
*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ጠቅላላውን ንግግር ደግመው ያዳምጡ እና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Fiona***
*Hi, how much is this jacket?*

***Shop assistant***
*That jacket's £59.99.*

***Fiona***
*Can I try it on?*

***Shop assistant***
*Of course you can.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! አሁን ሸመታ ላይ ሲሆኑ የዕቃዎች ዋጋ ስንት አንደሆነ መጠየቅ ይችላሉ። የተማሩትን መለማመድ አይርሱ። ጓደኛ ይፈልጉና 'How much is this?' የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ ይለማመዱ። ለተጨማሪ የ Essential English Conversation ክፍሎች በሚቀጥለው ዝግጅታችን ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018